# ታላቅ መንፈሳዊ ጉባዔ በመዲናችን ተከናውኗል

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን

ቸርነቱ ለማያልቅበት አደናይ ክብር ምስጋና ይግባውና ሰሞኑን በመንፈሳዊ ሕይወት ሙላት ተጥለቅልቀን ሰንብተናል። ልዑል እግዚያብሄር የተመሰገነ ይሁን!....

ኦስሎ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሰበካ ጉባዔ ያዘጋጀው 11ኛው አውሮፓ አቀፍ ጉባዔ በታላቅ መንፈሳዊ ግርማና ድባብ እንደተመላ በድል ተጠናቋል። አስሎ የሚገኘው የቅዱስ ገብርዔል ደብር አስተዳዳሪ ደጉና ቅኑ መላከ ጸዮን አባ አብርሃም በእንኳን ደህና መጣችሁ መንፈሳዊ ንግግር ዓርብ ሰኔ 20 ቀን 2000 ዓ.ም.(27.06.08) ከጠዋቱ አራት ሰዓት የተከፈተው ይህ ጉባዔ፤ ለሶስት ቀናት ያህል በታላቅ ድምቀት ተካሂዷል። በነዚህ የጉባዔው መሰተንግዶ እለታት፤ የበቁ የሃይማኖት አባቶች፣ ሊቀ ጠበብት ምመህራን፣ ሊቀ መዘምራን፣ መሪ ጌቶች፣ ጥልቅ እዝነ ልቡና ያላቸው አስተዋይ ቀሳውስት፣ ዲያቆናት፣ የሰበካ ጉባዔው ትጉህ አመራር አባላት፣ ከኖርዌይና ከተለያዩ ያለም ክፍሎች የመጡ ትሁት ኢትዮጵያውያን ምእመናን፣ አረጋውያን፣ እናቶች፣ ወጣቶች፣ ሕጻናትና ጥሪ የተደረገላቸው ኖርዌጂያን ተገኝተዋል። ከአውሮፓ የምእመናኑ፥ የመምህራኑና የቀሳውስቱ አመጣጥ (ባብዛኛው) ከስዊድን፥ ከፊንላንድ፥ ከዴንማርክ፥ ከቤልጅግ፥ ከኦስትሪያና ከኢጣሊያ ሲሆን፤ በመምህርነትና በሊቀ መዘምርነት ከካንዳና ካሜሪካ ሁለት የቤተ ክርስቲያኒቱ ታላቅ አገልጋዮች ተገኝተዋል። ከኖርዌይ የተለያዩ ከተሞች ጉባዔውን የተቀላቀሉና ታላቅ ድምቀትን ለማጎናጸፍ ለኦስሎ ወርተረኞች የተመቹት፤ እስታቫንገር፥ በርገን፥ ክርስቲያን ሳንድ፥ ትሮምሶ፥ ትሮንድሃይም ወዘተ... ናቸው።

በዚህ ጉባዔ የመክፈቻ ሥነ ሥርዓት ላይ ቫልገርድ ስቫርስታድ ሃውግላንድ የኦስሎ ቤተክርስቲያኖች ዋና ኃላፊ መገኘታቸውም፤ ለጉባዔው ድምቀት ተጨማሪ ግርማ ሞገስን ያከለ ከሞሆኑም በላይ፤ የኖርዌይን መንግሥት በጎ እሳቤና ድጋፍ ለማግኘታችን ዐይነተኛ ምልክት ሆኗል። ለክርስቶስ ቤተሰብ ልጆች ሁሉ መንፈሳዊ ጸጋን የተመላበት፤ ያብሮነት፣ የመከባበር፣ የመፈቃቀርና የመተዛዘን መንፈሳዊ ድባብ የረበበት ታላቅ ጉባዔ ሆኖ በመጠናቀቁ የሁላችን ልብ ባምላካችን ቸርነት ተመልቷል።

በዚህ ታላቅ አውሮፓ አቀፍ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ጉባዔ ላይ ከቀረቡት ብዙ ዓይነት ዝግጅቶች መካከል የሚከተሉት ጥናታዊ ጽሁፎች፣ ትምህርቶችና ትእይንቶች ለናሙና ያህል ይጠቀሳሉ። ቀሪውን የተሟላ ዝርዝር የዝግጅቱን ምላትና ስኬት ሰበካ ጉባዔው በዘገባ መልክ ሊያቀርበው ስለሚችል አልፈዋለሁ።

1. ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንና ጥናታዊ ጽሁፍ ....በቀሲስ አሸናፊ (ከኦስትሪያ)
2. “አይዟችሁ አትፍሩ እኔ ነኝ”፣ ”ልብስዎ ላዲስ ብእሲ”፣ “የመላእክት እንጀራ ሰው በላ” ... በመምህር አንዱዓለም (ከካናዳ)
3. “ክርስትናና ዘመናዊ ሕይወት”፣ “ዓሥራት በኩራት”፣ “ክርስቲያናዊ ጋብቻና የሕጻናት አስተዳደግ”... በቀሲስ መዝገቡ (ከቤልጂዬም)
4. “ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር”.... በቀሲስ ብሩኬ (ከስዊድን)
5. “የንስሃ ሕይወት” እና ለምእመናን የተለያዩ መንፈሳዊ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት... በሊቀ ትጉሃን ቀሲስ ጌጡ (ከስዊድን)



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

እኒህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ርእሳነ ትምህርቶችና ጥናታዊ ጽሁፎች ከብዙ ብዙዎቹ ዝግጅቶች መካከል ቢጠቀሱም፣ ቀሪዎቹን ዝግጅቶችና መስተንግዶዎች በመዘንጋት አይደለም። ከዚህ ሁሉ ጀርባ ባሜሪካን አገር ነዋሪ የሆኑት የሊቀ መዘምራን ይልማ ኃይሉ በመሰንቆ የታጀቡ መንፈሳዊ መዝሙሮች ለአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች ታላቅ የመንፈስ ምግቦች ሁነው ሰንብተዋል። ሊቀ መዘምራን ይልማ የድምጻቸው ቅላጼ፣ የመሰንቋቸው አቀኛኘት፣ ያንደበታቸው እርጋታና የመንፈሳቸው ምላት ሁላችንንም በተመስጠ ከዔዶም ገነት ደጃፍ እያደረሰ የሚያመላልሰን መለኮታዊ መንኮራኩር ነበር። እኒህን ከልብሰ ተክህኖአቸው ጀምሮ የደበቡ፡ የደረቡ ወንድም አምላክ በኪነጥበቡ ለዚህ መልካም ግብራቸው ባርኮ፡ ቀድሶ ወዲህ ዓለም ያመጣቸው ለመሆኑ፤ ላንዲት አፍታ ያወጋቸውና ያስትዋላቸው ምእመን አይስተውም። ፈጣሪ ለኒህ ወንድም ዝማሬ መላእክትን ያሰማልን!...

ወንድም ይልማን ካነሳሁ ዘንዳ የኛውን (የኖርጌውን) ምሁሩን መሪ ጌታ ደምለውን ማስለጠቅ ዘገባዬን ምሉእ ያደርገዋል። እኚህ የኛው መሪ ጌታ ለካስ ባለ ብዙ ዘርፍ ሙያተኛ፡ ሊቀ ጠበበት ኑረውን!... ወይ አለማወቅ!... ያን ሁሉ ምእመንና የሃይማኖት ጎምቱ ሁላ በቅዱስ ያሬዳዊ ዜማ፣ ወረብና ሽብሸባ ይዘውት የት ጥርግ እንዳሉ ታውቃላችሁ?... በቀጥታ አገር ቤት.... ከዚያም አክሱም ከያሬድ ዜማዊ አምባ... ከዚያም ሽቅብ ወደ መንግሥተ ሰማየ ሰማያት.... ጭልጥ ብለን ጠፋን!!!!!!!!!!!!!!!! ተመስገን ነው... ይህን በረከት በማግኘታችን። ደሞም ዝማሬው፡ ሽብሸባውና ወረቡ ላይ የተሳተፉት የኦስሎዎቹ መዘምራን ቅልጥፍና.... አቤት የሰው ልጅ ሥልጠት አስኝቷል። እኚሁ መሪ ጌታ ደምለውም ሳይሆኑ አልቀሩም እንዲህ ከሽነው አሰልጥነው ለፍሬ ያበቁዋቸው!... ድንቅ ጥበብ ድንቅ ሥራ ተሠራ እናንተዬ... ለጌታ ምስጋና ይግባው! ሊቀጠበብት፡ መሪ ጌታ ደምለውንና ደቀመዛሙርቱን ቸርነቱ የማያልቅበት ልዑል እግዚያብሄር ዝማሬ መላእክት ያሰማልን። እኒያ የኦስሎ መዝሙርተኛ ሕጻናት፥ የእስቶክሆልም መዘምራን፥ የፊንላንድ አነስታይ ገዝ መዘምራን፥ የስታቫንገር መዘምራን፥ የትሮንዳይም መዘምራን፥ ያውሮፓ አቀፍ መዘምራንና ሌሎችም ሁሉ ያቀረቧቸው መንፈሳዊ ጣዑመ ዜማዎችና ሽብሸባዎች ለጉባዔው ፈርጥና ጌጡ ሲሆኑ ለአምላክ ደሞ የመከበሪያውና የመመስገኛው ልሳኑ ነብሩ። ለነሱም ሞልቶ ከተረፈው ጸጋና በረከቱ አብዝቶ ይስጥልን፤ ዝማሬ መላእክትም ያሰማልን። ደሞም አንድ ቀን መሪ ጌታ ያቺን የቋጠሩልንን ስለእመቤታችን የምታውሳ (በጊዜ እጥረት ምክንያት ያልቀረበችውን) ትምህርት አንድ ቀን "እነሆኝ..." ይሉን ዘንድ ተስፋዬ ነው።

እንግዲህ ይህ መንፈሳዊ ጉባዔ በጣም በጣም ለረዥም ሰዓቶች በየቀኑ ሲካሄድ፤ ማነው ለዛና ጣእም እየሰጠው ተናፋቂና ተወዳጅ እንዲሆን ይበልጥ ያዋዋው? ያጣፈጠው? የሚል ትሁት ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም። መልሱ ባንደኛነት ያባ አብርሃም ደግ፡ ቅን፡ ትሁት መስተንግዶና አመራር ነው የሚል ሲሆን፤ በሁለተኛነት የሊቀ ትጉሃን ጌጡ አባታዊ ሚና የሚጠቀስ መሆኑ አይቀሬ ነው። አባ አብርሃም ባባታዊ ትህትናቸውና ፍቅራቸው የሚንከባከቡትን የጉባዔውን ተሳታፊ ምእመን፣ ሊቀ ትጉሃን ጌጡ ይረከቡና ባባታዊ ለበቃቸው እየሸነቆጡ ሁሉንም ልክ ልክ ያስገቡታል። ድንቅ ተሰጥኦ!... ያምላክ በረከት ይሉታል እንዲህ ነው። "የሚያበላ መስሎ የሚሸኝ እንግዳ..." ይሉ ዘንድ በዓለማውያን ቤት፤ ቄስ ጌጡም ያሳቁ ያጫወቱ መስለው የሚያስተላልፉት መንፈሳዊ ትምህርት ምጸቱ (the irony) ውስጥን ደህና አድርጎ ያስፈትሻል። የማስታወስ ችሎታቸው ከሚያቀርቡዋቸው የሕይወት ተሞክሮ ምሳሌዎች አኳያ ሲመዘኑ፤ እጹብ ድንቅ አስተማሪ ያሰኛቸዋል። እንዲያው ኖርጌን በቅኝ ግዛት አባትነት ብቻ መግዛታቸው ከፋኒ፣ እሳቸውስ ታምባችን ተመንደራችን ተቀዬያችን ላፍታም መጥፋት አልነበረባቸውም። እንዲህ ባቋማቸው አምጸው ከጸኑ አንድ ቀን ፈንጋይ ግብረ ኃይል ልከን በኖርጌ ቁጥጥር ስር ማድረጋችን እማይቀር ነው። ተያ በኋላ ማን በድሮ በሬ እንዳረሰና እንዳላረሰ ለስዊድኖች እኛ ኖሽኮች እናሳያቸዋለና!.....ቅቅቅቅቅ እኒህ እኒህን የመሳሰሉት አባቶች ትምህርታቸው፣ ተመክሯቸው፣ ለዛቸው... መንፈስን የሚያለመልም የሕይወት ቅመም ሥሪት ነው። አምላክ ቃለ ሕይወት ያሰማልን!...



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ወደ ሰበካ ጉባዔው ታላቅ ገድልና አፈጻጸሙ ስንመለስ፤ ሰብሳቢውን ትሁቱን አባ አብርሃምን፣ ወንድም ደነቀን፣ ኮከብ ግጥሚን አይዋ ተክሌን፡ እታለም ሰሎሜን፣ ወንድም ታደለንና አንዱዓለምን ማስታወሳችን የግድ ነው። እማን ላይ ሆነሽ ማንን ታሚያለሽ እንዳይሆን ነገር ነገሩ፤ አስቀድመን ለእነሱ ረዥም እድሜና ጤና እንመኝ። ይህ የበቃ የነቃ ያመራር ችሎታችሁ በነካ እጃችሁ አንዲት የመሰባሰቢያ አጸድ ያላት የቤተ ክርስቲያን ጎጆ እንቀልስ ዘንድ የሙሴን በትር እንደያዛችሁ ምሩን ልንላቸውም ይገባል። ተሰው ቤት አውጡን ለማለት ነው። እኛ ባገራችን ባምባችን ባውጋራችን ታቦታችን ለጥምቀት ታልሆነ በቀር ተቤታችን ወጥቶ ከባእድ ቤት አድሮብን አያውቅምና፤

“ጎበዝ እንበርታ፥ እንረዳዳ
እኛ ምን አለን፥ ተሰዉ ጓዳ
ታቦት አይወድም ባዳ
ምሰሶው ይቁም፥ ይታይ ተራዳ
አንተው ነህ ከፋይ፥ የራስክን እዳ
የ’ምነትክን ጉማ፥ የምድርን ፍዳ፤
ጎበዝ በርታ በል፥ ገብርዔልን ይዘህ
ተክልዬን ምርኩዝ፥ መሰላል ብለህ”

ድር ቢያብር አምበሳ ያስርን ደሞ ያው በቀደም አሳይታችሁናልና በሱ በጌታ ፈቃድ የማይቻል የለምና ይቺን ትንሽ ምድራዊ ግብር እንፈጽማታ! ለማንኛውም ሥራችሁን ሁሉ አምላክ በበረከቱ ይባርክ!...

የሰበካ ጉባዔውን አደራ ተረክቦ ይህን ታላቅ አውሮፓ አቀፍ ጉባዔ አዘጋጅቶ፤ በመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ ታድመን ነፍሳችንን እንድንታደጋት ያደረገን ማነው? የሚል ጥያቄ ደሞ መከተሉ አይቀርም። አዎን መልሱ ቅርብ ነው። በመጋቢ ዮሃንስ ታዬ የሚመራውና አይዋ ካሳሁን፣ አይዋ አብርሃም፣ እታታ በላይነሽ፣ አይዋ ተሾመ፣ እታታ ዔልሳቤጥ፣ አይዋ ተክሉ የተካተቱበቱ የጉባዔው አዘጋጅ ኮሚቴ ያንበሳ ድርሻውን ምስጋና ታንድ የኔ ብጤ ትሁት ምእመን ቢያገኝ ቲያንሰው እንጂ ቲበዛበት አይሆንም። አቤት ያዳራሽ ምርጫችሁ ስኬት ማስደሰቱ ወገኖቼ... ለኔ ብጤው የሩቅ አገር እንግዳ ዘኬው እዚያው... መኝታው እዚያው... መጠጡ እዚያው... ሻይ ቡናው እዚያው... ትምርቱ፥ መዝሙሩ፥ ሱቁ (ያውም ሱቅ በደረቴ ጭምር) አውደ ትእይንቱ ... ወዘተርፈፈፈፈፈፈ... እዚያው በዚያው የተሟላለት መስተንግዶና ዝግጅት በማድረጋችሁ ምን ያህል አንድዬ ከናንተ ጋር እንደቆመ ለማስተዋል ለማንም የተሰወረ አይሆንም። ሁሉንም በሰዓቱ እያቀረቡ ያን ሁሉ ለቁጥር የሚያስቸግር ምእመን ማስተናገድ መቻል ልዩ ያምላክ ረድዔትና ጸጋን መታደል ነው።

እናም አደናይ ታድጓችሁ በርትታችሁና ጠንክራችሁ በቤተ ክርስቲያናችን ስም ቁማችሁ ተከታይ ምእመናንን በክርስቲያናዊ ምግባራችሁ ሰላኮራችሁ እኛም በናንተ መኩራታችንን “እንሆኝ...” እንላለለን። ያንን አማርኛችንን እንደ ቶርባናሼ የምንጭ ውሃ ግጥም አድርጎ ከነእንጥፍጣፊው የጨለጠ የኖርሽክ ደብተራ፤ አይዋ አርነን፤ ሌላ ቀን ደሞ አቶ ካሳሁን አስመጥቶ፤ መልእክተ ዮሃንስን በግእዝ፥ በውርደ ንባብና በንባብ ወጥቶ ይወርደው ዘንድ አንድ እንድትሉት ትንሽ አደራ አለችኝ።

ሊቀ ትጉሃን ጌጡ “አይበቃውም? ይበቃዋል...” እያሉ ለቀረበላቸው መጠይቅ ሁሉ ማሰሪያ እንዳበጁለት ሁሉ፤ እኔም “አይበቃውም? ይበቃዋል...” ብዬ ላሳርጋ... በዚሁ ላብቃ። የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተኛ ሁሉ ዛሬም እንደትናንቱ እንደጥንቱ የእምነት ትጥቁን ተልቡ አኑሮ፣ የመንፈስ ጽናቱን ድግ አጥብቆ፤ ጸረ ሃይማኖቶችንና ጉግ ማንጉጎችን ትጥቅ ማስፈታት



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com

ይጠበቅበታል። የልዑል እግዚአብሄርን ታላቅነትና አባትነት ለአህዛቦችና መናፍቃን ሁሉ በጽናት ቆሞ ማሳየት ያስፈልጋል።

ልዑል አምላካችን አገራችንን ኢትዮጵያን ይባርክ!
ልዑል እግዚያብሄር ልባችንን በመንፈስ ቅዱስ ይሙላ!
በሃይማኖታችን እንደምቃለን እንኮራለን!

(*በአበራ ለማ፣ ተጣፈ በእለተ ሰኞ፣ ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ. ም.)



PDF Created with deskPDF PDF Writer - Trial :: http://www.docudesk.com